# ሜ/ጀኔራል አምሃ ደስታ (1932 – 1981) ሰባተኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይል አዛዥ

ምንጭ - የኢትዮጵያ አየር ኃይል (1921-1983)



ሜ/ጀ አምኃ ደስታ በ1932 ዓም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በሊሴ ገብረማርያምና በኋላ ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታተሉ ። በ1949 ዓም በአውሮፕላን መካኒክነት ሙያ አየር ኃይልን ለማገልገል ተቀጥረው ሥልጠናውን ጀመሩ ። አምሃ ለመካኒክነት ቢቀጠሩም ቴክኒክ ት/ቤት የሚሰጠውን ትምህርት በመከታተል ላይ እንዳሉ በራሪ የመሆን ፍላጐታቸው እየጨመረ መጥቶ ወደ በረራ ት/ቤት የሚያስገባውን ፈተና ወስደው በጥሩ ውጤት ስላለፉ በበረራ ኰርስ ፒ - 9 የበረራን ሥልጠና እንዲከታተሉ ተመረጡ ።

ጀ/ል አመሃ በረራ ት/ቤት ገብተው ለትንሽ ጊዜ ያህል እንደተከታተሉ በ1950 ዓም ለከፍተኛ የበረራ ሙያ ኰርስ ከጓደኞቻቸው ጋር ወደ አሜሪካ ተላኩ ። በአሜሪካ አገርም የበረራ ትምህርት በ ቲ-34 ፣ ቲ-37 ፣ ቲ-33 ፣ እና በተዋጊው አውሮፕላን በኤፍ-86ኤፍ ሁለት ዓመት የፈጀ ሥልጠና ወስደው በውጤታቸው ተመስግነው በ1953 ዓም ወደ አገራቸው እንደተመለሱም የም/መ/አ ማዕረግ አገኙ ።

ከዚያም በረራ ት/ቤት በአስተማሪነት ተመድበው የአሜሪካኖችን ሲስተም ለኢትዮጵያ አየር ኃይል ማሰልጠኛ ተቋም ካስተዋወቁት አስተማሪዎች አንዱ ነበሩ ። በበረራ ሥራ በየስኳድሮን እየተዘዋወሩ ካገለገሉ በኋላ የሻምበል ማዕረግ እንደደረሱ ለስኳድሮን አዛዥነት ኰርስ እንደገና ወደ አሜሪካን አገር ተልከው ኰርስ በመካፈል ባገኙት ከፍተኛ ውጤት ብቸኛው የውጪ አገር ተማሪ ሆነው ከሌሎች አሜሪካውያን የኰርስ ተሳታቺዎች ጋር “ተደናቂ ተመራቂ” (Distinguished graduate) በመሆን ተመረቁ ። ት/ቤቱ የነበሩት አሜሪካውያን መምህሮቻቸውና አብረዋቸውም ኰርሱን የተሳተፉ ሁሉ የአመሃን የትምህርት መቀበል ክህሎት በማድነቅ “ትምህርቱን አገርህ ተምረህ ነው ወይ የመጣኸው” ? እስከ ማለት ደርሰው ነበር ።

ከዚያ በኋላ ጀ/ል አመኃ በተለያዩ የሥራ ኃላፊነቶች እየተመደቡ በሥራቸው ምሳሌ እየሆኑና እየተመሰገኑ ከማዕረግ ወደ ማዕረግ እያደጉ ጀኔራል ማዕረግ የደረሱ የሚደነቅ ችሎታ የነበራቸው መኰንን ነበሩ ። የብዙ ዓመት የበረራ አገልግሎታቸው በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ወደ ተለያዩ ውጪ አገሮችም ወስደዋቸዋል ። ለዚሁ አገልግሎታቸውም የተለያዩ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሽልማቶችና ሜዳዮች የተሰጣቸው ሲሆን ፤ ከኩንጌ መንግስትና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተሰጧቸው ሽልማቶች ቀዳሚ ሆነው ይገኛሉ ። በሃገር ውስጥም በተለይ በ1969 ዓም ከተስፋፊው የሶማልያ መንግስት ጋር በተደረገው ጦርነት የአገርን ዳር ድንበር ለማስከበር ላሳዩት ተጋድሎ የላቀ የጦር ሜዳ ጀብዱ ሜዳይ ያበቃቸውን የጦር ሜዳ ውሎ አጥኚ ኩሚቴው የፃፈላቸው የምስክርነት ቃል እንዲህ ይነበባል ። .... " ምንለው ሁሉ እውነትና በግብር የተሰራ ነው ። ኩ/ል አመኃ ደስታ የምስራቁ ጦርነት ሃምሌ 1969 ዓም በተከፈተበትና የበራሪዎች ዕጥረት በነበረበት ጊዜ ፋታ ሳይገኝ እስከ አምስት ሶርቲ (የምልልስ በረራ) በቀን በመብረር ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጓል ። ይኸውም በጌዴ ፣ በደጋሃቡር ፣ፊዲስ ፣ ጂጂጋ ፣ ቆሬ ፣ ኩምቦልቻ ፣ ኤጄርሳ ጎሮ ፣ ሃራዋ ፣ ጀልዴሳ ፣ አነሮና ባቢሌ ግንባሮች ሲሆን ፤ በተለይም የጠላት ድርጅቱን የመደበቅ ከፍተኛ ችሎታ የነበረውና አካባቢውንም በተጠናከረ የአየር መቃወሚያ መሳሪያ ቢያጥርም የሃገርን አንድነት ከራሱ በማስቀደም ሚሳኤልና ሺላካ ሳያግደው ተነፃፃሪ የሌለው ተጋድሎ አድርጓል ።



" ሃምሌ 9 ቀን 1969 ዓም የሶማልያ ጦር የድሬዳዋ አየር ጣብያን ለመያዝ በተቃረበበት ጊዜ ከደብረዘይት እየተነሱ በመመላለስ ጠላትን በመደብደብ ጠላት ተዳክሞ ወደ ኋላ እንዲመለስ ካደረጉት በራሪዎች መካከል ጀ/ል አመሃ አንዱ ነበሩ ። ነሃሴ 6 ቀን 1969 ዓም የጅሬን የጦር ሰፈር ሶማልያ ውስጥ ገብተው እንዲመቱ ከታዘዙት በራሪዎች አንዱ በመሆናቸው በረራውን በመምራት ወድ ዒላማው በሚሄዱበት ጊዜ ከ100 የማያንሱ ተሽከርካሪዎች ያለው ኮንቦይ ከጅሬ ወደ ሃረሪት ሲያመሩ በመታየታቸው የተሻለ ዒላማ መሆኑን በመገንዘብ አብረዋቸው ለነበሩት በራሪዎች ጉዳዩን ካስታወቋቸው በኋላ ፣ በያዙት መሳሪያ ስልሳዎቹን ተሽከርካሪዎች ከጥቅም ውጪ በሚያደርጉበት ወቅት ጀ/ል አመሃ ኃላፊነቱን በመውሰድ ጥቅቱን ፈፅመዋል ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com




“ ሃምሌ 10 ቀን 1969 ዓም ጠላት እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ የድሬዳዋን ከተማ ለመያዝ በታንክ ፣ በመድፍና በብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በጣም በርካታ በሆነ ፀረ አውሮፕላን መሳሪያ ተጠናክሮ በመጣበት ጊዜ ፣ የአየሩ ሁኔታ ከሰዓት በኋላ ዘግይቶ ሲሻሻል ያለ አፍታ ዕረፍት ከአንዱ አውሮፕላን ወደ ሌላው ዘሎ በመግባት አውሮፕላን በመቀያየር ቀኑ ከመጨለሙ በፊት ያልተቆጠበ ተጋድሎ አድርጓል ።

“ በነሃሴ 1969 ዓም ጠላት የጂጂጋን ከተማ ለመያዝ በመጣበት ጊዜ ወገንን ለመከላከልና ከተማይቱን ለማዳን በዝቅተኛ ከፍታ በመብረር ከጠላት ጋር የጨበጣ ያህል ተዋግቷል ።...”

እንግዲህ በወቅቱ ተመርጦ የነበረው ኰሚቴ ስለ አመኃ ደስታ ተሳትፎ ከጦርሜዳ የተሰበ አለሰበውን መረጃም በመጠቀም ለሽልማቱ እንዲበቃ ምስክርነቱን በዚህ መልክ ነበር የሰጠው ።

ጀ/ል አመሃ ደስታ በሰሜኑ ጦርነትም በተዋጊ በራሪነት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል ። የኢትዮጵያ ጦር ባደረጋቸው ብዙ እንቅስቃሴዎች የአየር ድጋፍ ሰጥተዋል ። ባሬንቱ አካባቢ ባደረጉት አንድ በረራ ጠላትን አጥቅተው ሲወጡ አውሮፕላናቸው ተመትቶባቸው ከቁጥጥር ውጪ ስለሆነ ዘለው በመውጣት በፓራሹት ወገን መሃል አርፈው ሊድኑ ችለዋል ። ከዚህ በኋላም በሄሊኰፕተር ወደ ጣቢያቸው በመመለስ የሃኪም ዕረፍት ሳያስፈልጋቸው ወዲያውኑ ወደ ውጊያ ሥራቸው በመመለሳቸው ከሰራዊቱ ከፍተኛ አድናቆትን አትርፈዋል ።

ሜ/ጀ አመሃ ደስታ ሃቀኛና ያመኑበትንና የተሰማቸውን ከመናገር ወደ ኋላ የማይሉ መሆናቸው ይነገርላቸዋል ። ለዚህ ዋቢ ከሚሆኑት አንዱ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣኖችን አስከትለው ባህር ዳር አካባቢ የነበሩ የጦር ክፍሎችን ጐብኝተው ገለፃ ከተደረገላቸው በኋላ ማምሻውን ወደ ሆቴላቸው ተመለሱ ። በድካም ላይ የነበሩት ባለሥልጣኖች በመዝናናት ላይ እንዳሉ ፕሬዝዳንቱ መጥተው ከፍ ባለ ድምፅ “ጓዶች ዛሬ ብዙ ስንሰማና ስንታዘብ ውለናል ፤ ታድያ ችግራችን ምንድነው ? እስቲ በግልፅ እንነጋገርበት” በለው ባለሥልጣኖቻቸውን ለውይይት ጋበዙ ። ለጊዜው ሁሉም ፀጥ አሉ ፤ ወደ ጐን መተያየትም ተጀመረ ። መጨረሻ ጀ/ል አምሃ እጃቸውን አውጥተው የሚሰማቸውን በሙሉ ዘረዘሩ ። ፕሬዝዳንቱ እጅግ ከመናደዳቸው የተነሳ ጥለው ለመሄድ ሲቃጡ ቆዩና መጨረሻ ላይ ብድግ ብለው “ምዕራብ ከተማራችሁ ምን ይጠበቃል” ? ብለው እራት ሳይበሉ ገብተው ተኙ ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ፕሬዝዳንቱ እንደሄዱ ጀ/ል ኃይለጊዮርጊስ ጀ/ል አምሃን ተጠጉና "ጓድ አምሃ ፣ ለንጉስ የሚነገረው እንዲሰማው የሚፈልገውን እንጂ ነገሩን መለደፍ አይደለም ብለዋቸው አለፉ ። ጀ/ል አመሃም ያመኑበትን ፣ የሚሰማቸውንና ሃቁን ተናግረው ስለነበረ "እንግዲህ በሀቅ እንነጋገርበት አለ ፤ ያለውን ነግሬዋለሁ" ብለው ለሌሊቱ ተለያዩ ። በማግስቱ ጧት ጀ/ል አምሃና ጀ/ል ተስፋዬ ገብረኪዳን ሲገናኙ ጀ/ል ተስፋዬ በፈገግታ "አዬ አምኃ .. ወንድ ነሽ እኮ ፤ ትናንት የተናገርከው እኮ ትክክለኛውን ነገር ነው ። ይህንን እኛ አብረነው የምንውለው መናገር ያለብን ነበር ፤ ግን ምንያደርጋል ሁላችንም ፈፊዎች ነን ። አይዞህ እኔ ለቁርስ ከመምጣቱ በፊት ገብቼ አነጋግረዋለሁ ብለው ወደ ፕሬዝዳንቱ ክፍል ገቡ ። ፕሬዝዳንቱና ጀ/ል ተስፋዬ ቆይተው ሲመጡ በከፊል ፈገግታ ጀ/ል አመኃን "ነገርከን አይደል" ብለው አለፏቸው ። የጀ/ል ተስፋዬ ዘዴ እንደሰራ ሁሉም አመኑ ። እንዲያውም ከዚያ አልፎ አምኃ ወዲያው የሜ/ጀ ማዕረግ ተሾሙ ።

ይህ የባህር ዳይ ክስተት ጀ/ል አምኃ ስለ ፕሬዝዳንቱ የነበራቸውን በጐ አመለካከት ለዘለቄታው የለወጠ እንደሆነ ታውቋል ። ስለሆነም በ1981 ዓም ኩዴታ የዕለቱ ዕለት ተነግሯቸው ሳያወላውሉ ተስትፈዋል ። ቀደም ብሎ ስለመፈንቅለ መንግስቱ ያልተነገራቸው ምንዓልባት ቀደም ሲል ስለፕሬዝዳንቱ በነበራቸው በጐ አመለካከት የሚጠረጠሩ ሰው አድርጓቸው ይሆን ? ወይስ እንደተባለው ስለመንግስት ግልበጣ አድማ እንዲነግራቸው የተላከው ሰው እውነትም ሊያገኛቸው ስላልቻለ ሳይሰሙ ዘግይቶ ነው ?



መፅሃፍ ለማንበብ ባላቸው ከፍተኛ ፍቅር ፣ በቼዝ ጨዋታ ፣ በቴኒስና በቅርጫት ኳስ ባላቸው ድንቅ ችሎታ የሚታወቁት ሜ/ጀ አምኃ ደስታ በተዋጊነት ፣ በበረራ አስተማሪነት ፣ በምድብ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አዛዥነት ፣ በአየር ኃይል ምክትል አዛዥነትና በመጨረሻም በአየር ኃይል ዋና አዛዥነት ኢትዮጵያን ያገለገሉ ፍፁም ሃገር ወዳድ ፣ ትጉህ ፣ ብልህና ቅን የአየር ላይ ጀግና ነበሩ ። ከታሪክ እንደምናነበው ብዙ ለኢትዮጵያ የደከሙ ፣ የደሙና ቅን ያሰቡ ዜጐች መጨረሻ ሳያምር ቀርቷል ። የሜ/ጀ አምኃ ፅዋም ከዚህ አልተለየም ። አምኃ አገሪቱን ከጦርነት ለማውጣትና ወደ ልማት እንድታተኩር ለማድረግ በተሞከረው የግንቦት 1981 ዓም መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተሳትፈው መክሸፉን እንደተረዱ ውርደትን በመጠየፍ በመከላከያ ሚኒስቴር የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ እራሳቸውን አጥፍተዋል ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com